የሰ/መ/ቁ. 48997

ጥቅምት 16 ቀን 2003 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** የቦሌ ክ/ከ/ገቢዎች መምሪያ ነ/ፈጅ ታደሰ አንዳርጌ - ቀረቡ፡፡

**ተጠሪዎች፡-** 1. አቶ መዓዛ ሽፈራው - ጠበቃ ወርቅነሽ መንግሥቱ - ቀረቡ፡፡

2. ወ/ሮ ስብለ ከፈለኝ - ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ አቤቱታ የቀረበው በተጠሪዎች መካከል የንብረት ክፍፍል ከመደረጉ በፊት የቀዳሚነት መብት ይፈጽምልኝ ሲል አመልካች ያቀረበውን አቤቱታ የሥር ፍ/ቤቶች ባለመቀበላቸው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ይታረምልኝ በማለት አመልካች ስለጠየቀ ነው፡፡

አመልካች ለሰበር ችሎቱ ያቀረበው አቤቱታ ይዘት ሲታይ 1ኛ ተጠሪ በኮንስትራክሽን ሙያ የተሰማሩ ነጋዴ ስለመሆናቸው፣ አመልካችም በአዋጅ ቁጥር 286/94 እና 285/94 መሠረት የንግድ ትርፍ ገቢ እና ተጨማሪ እሴት ታክስ ከ1997 እስከ 2000 ዓ.ም. ያለባቸው የመንግሥት እዳ ብር 405,070.88 እንዲከፍሉ ማስታወቂያ ደርሷቸው ባለመክፈላቸው በአዋጅ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ለማስፈጸም እንደሚችል፣ 1ኛ ተጠሪ በተጨማሪ እሴት ታክስ የሰበሰቡት ገንዘብ ብር 40,140.63 ጭምር መታገዱን በመግለጽ ይህንኑ ለማስፈጸም ያቀረበውን የጣልቃ ገብነት አቤቱታ የሥር ፍ/ቤት አለመቀበሉ ስሕተት ነው ተብሎ እንዲታረም በሚል ነው፡፡

የሰበር ችሎቱም የአመልካች አቤቱታ ውድቅ የተደረገው በሕጉ አግባብ ነው ወይንስ አይደለም? የሚለውን ለመመርመር ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡ አዟል፡፡

1ኛ/ ተጠሪ በ24/06/2002 ዓ.ም. ባቀረበው የጽሁፍ መልስ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር በነበረው ክርክር ንብረቶቹ በመታገዳቸው የመንግሥት እዳ /ግብር/ ለመክፈል አለመቻሉን ገልፆ በዚህም ምክንያት የሥራ ፈቃዱም እንዳልታደሰ በመዘርዘር የሥር ፍ/ቤት ትዕዛዝ እንዲታረም ጠይቋል፡፡

2ኛ ተጠሪ በበኩሏ በ18/5/2002 ዓ.ም. የተፃፈ መልስ አቅርባለች፡፡ ይዘቱም የአመልካች አቤቱታ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 418 መሠረት ተቀባይነት እንደሌለው ከ1ኛ ተጠሪ የሚፈለገው

የግብር ገንዘብ መጠን በ1999 እና 2000 ዓ.ም. የተከፋፈለ በመሆኑ ተጠሪዋ ደግሞ ከ1ኛ ተጠሪ ጋር የነበራት ግንኙነት በ1999 ዓ.ም. የተቋረጠ በመሆኑ የጋራ እዳ ሊባል እንደማይገባ በዚህም ምክንያት የጋራ ሀብት ሊያዝ እና ሊፈፀምበት እንደማይገባ በመዘርዘር የሥር ፍ/ቤት ትእዛዝ እንዲፀና ጠይቃለች፡፡

አመልካች ክርክሩን በማጠናቀር የመልስ መልስ ሰጥቷል፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኙ ክርክር ከፍ ሲል የተመለከተው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡

ከመዝገቡ እንደተረዳነው በ1ኛ ተጠሪ እና በ2ኛ ተጠሪ መካከል የንብረት ክፍፍልን በተወሰነው መሠረት አፈፃፀሙ በ2ኛ ተጠሪ አመልካችነት መዝገብ ተከፍቶ በሂደት ላይ ባለበት ሁኔታ ግራ ቀኙ ንብረቱን ከመከፋፈላቸው በፊት ከ1ኛ ተጠሪ የሚፈለግ ግብር እና ተጨማሪ እሴት ታክስ በቀዳሚነት ለማስፈጸም አመልካች አቤቱታ ያቀረበ ስለመሆኑ ነው፡፡

አመልካች ለአቤቱታው መሠረት ያደረገው መሠረታዊ ሕግ አዋጅ ቁጥር 285/94 እና አዋጅ ቁጥር 286/94ን ስለመሆኑ ግልጽ ነው፡፡

የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 32/1/ እና የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 80/1/ ላይ እንደተደነገገው ዋስትና የተሰጣቸው የሌሎች አበዳሪዎች የቅድሚያ መብት እንደተጠበቀ ሆኖ ታክስ ወይም ግብሩ ተከፍሎ እስከአለቀበት ጊዜ ድረስ ታክስ ወይም ግብር የመክፈል ግዴታ ያለበት ሰው ሀብት ላይ ባለሥልጣኑ ከማናቸውም ሌሎች እዳዎች የቀደምትነት መብት እንዳለው ተመልክቷል፡፡ በዚህ ረገድ የሕጉ አገላለጽ ግልጽ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ በተጠሪዎች መካከል ንብረት ክፍፍል እንዲደረግ መወሰኑን ተከትሎ የፍርድ ባለመብት የሆነችው 2ኛ ተጠሪ ባስከፈተችው የአፈፃፀም መዝገብ በ2ኛ ተጠሪ ስም አለ የተባለን ሀብት ያስከበረች ስለመሆኑ መዝገቡ ያስረዳል፡፡ በፍርድ ባለእዳ ጥያቄ የታገደና የተከበሩት የ2ኛ ተጠሪ ሀብቶች አንድም በዓይነት አልያም ተሸጠው ለፍርድ ባለመብት የሚከፈል መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ስለሆነም ንብረቱ ለፍርድ ባለመብት ከመከፈሉ በፊት አመልካች በሕግ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት መብቱን ለማስከበር እና ለማስፈጸም አፈፃፀሙን ለያዘው ፍርድ ቤት አቤቱታ ማቅረቡ ሲታይ ከሕግ የመነጨ መሠረት ያለው መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

አመልካች በአፈፃፀም በተያዘ ንብረት ላይ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 418 ጠቅሶ አቤቱታ ማቅረቡም ቢሆን በሥነ ሥርዓት ሕጉ እንደተደነገገው የቀዳሚነት መብቱን መሠረት /መነሻ/ ምክንያት ማስረዳት የሚጠበቅበት እንጂ በዋናው ውሣኔ እንዲከራከር አያስገድደውም፡፡

ስለሆነም አመልካች ያቀረበውን አቤቱታ የሥር ፍ/ቤቶች ውድቅ ማድረጋቸው የሕጉን ዓላማና ይዘት ያገናዘበ ባለመሆኑ ሊታረም የሚገባ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በሌላ በኩል 2ኛዋ ተጠሪ የጋራ አፈፃፀም አይመለከተኝም የሚል ክርክር በዚህ ሰበር ችሎት በአማራጭ አቅርባለች፡፡ በመሠረቱ ከ1ኛ ተጠሪ የሚፈለገው የተከሣሽ እና የግብር እዳ የግል ወይንስ የጋራ? የሚከፈለውስ ከግል ሀብት ወይንስ ከጋራ ሀብት የሚሉት እና ተያያዥ ጭብጦች በሥር ፍ/ቤት ተመርምሮ ውሣኔ ያልተሰጠባቸው ስለሆነ በዚህ ሰበር ችሎት የሚመረመርበት የሕግ አግባብ የለም፡፡

ስለሆነም በዚህ ረገድ ጉዳዩ እልባት ሊያገኝ የሚገባው የሥር ፍ/ቤት ተመልሶ ግራ ቀኙ በሚያቀርቡት ክርክር እና ማስረጃ መሆን እንዳለበት ታምኗል፡፡

ስለሆነም አመልካች ያቀረበውን የቀዳሚነት መብት ይከበርልኝ ጥያቄ የሥር ፍ/ቤት ሳይቀበል መቅረቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ በማረም ተከታዩን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 140988 በ05/08/2001 ዓ.ም. የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ በማድረግ የሰጠው ትዕዛዝ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይህንኑ ትዕዛዝ በመ/ቁ. 81055 ነሐሴ 11 ቀን 2001 ዓ.ም. በማጽናት የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የአመልካችን አቤቱታ ተቀብሎ የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶ ተገቢውን ውሣኔ እንዲሰጥበት ብለን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 343/1/ መሠረት መዝገቡን ለፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አፈፃፀም ችሎት መልሰናል፤ ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

# ልዩ ልዩ